<u>አስረኛው የአርብቶአደሮች ቀን የጋራ የአቋም መግለጫ</u>

እኛ የኢትዮጵያ አርብቶአደሮች ከጥር 17-18/2000 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት በአዳማ ከተማ ተገኝተን "የላቀ ቁርጠኝነት ለመልካም አስተዳደርና ለዘላቂ የአርብቶ አደር ልማት በአዲሱ የኢትዮጵያ ሚሌኒየም" በሚል መሪ ቃል የኢፌዴሪ መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር አቶ መለሰ ዜናዊ፣ የፌዴራልና የክልል ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት፣ የልማት ጀግኖች፣ የልማት አጋሮች እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (መያድ) በተገኙበት ለ10ኛ ጊዜ በደማቅ ሁኔታ አክብረናል፡፡

የዘንድሮ በዓል ለየት የሚያደርገው በአዲሱ የኢትዮጵያ ሚሌንየም ህዳሴዋን እውን ለማድረግና ደህንነትን ለመዋጋት ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ ባለበት ወቅት የላቀ ውጤት ላስመዘገቡ የልማት ጀግና አርብቶ አደሮችና አጋሮቻቸው ልዩ የክብር ሽልማት የተሰጠበት በመሆኑ ታሪካዊ ቀን መሆኑና ሁላችንም ለልማትና ለመልካም አስተዳደር ተግተን ለመስራት የሚያነሳሳ አበረታች ጅምር የታየበት መሆኑ ነው፡፡

በተለይም የኢፌዴሪ መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር አቶ መለሰ ዜናዊ ከዚህ ቀደምም ቃል እንደገቡት ሁሉ የኢትዮጵያ ህዳሴ በአዲሱ የኢትዮጵያ ሚሌኒየም ካለ አርብቶ አደሩ ቀጥተኛ ተሳትፎ ሊተገበር እንደማይቻል ማረጋገጣቸው የመንግሥት የላቀ ቁርጠኝነት መኖሩን ያመላከተ ነው፡፡

የአርብቶ አደሮች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች እጅግ ውስብስብ በመሆናቸው መንግሥት ፓሊሲዎችንና እስትራቴጂዎችን በማውጣት ችግሮችን ደረጃ በደረጃ ለመቅረፍ እያደረገ ያለው ጥረት የሚያበረታታ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቀደም ሲል በነበሩት ስርዓቶች ተዘንግቶ የነበረውን ችግር በጋራ በመወያየት የመፍትሔ አቅጣጫ እንድናስቀምጥና የበጐ ተሞክሮዎችን ልምድ እንድንለዋወጥ የጋራ መድረክ ተመቻችቶ በአገር አቀፍ ደረጃ በመከበሩ አርብቶ አደሩ በአዲሱ የኢትዮጵያ ሚሌኒየም ህዳሴውን የሚያረጋግጥበት አዲስ ምዕራፍ መሆኑን ያመላክታል፡፡

ስለሆነም እኛ የኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች ከጥር 17-18/2000 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት በአዳማ ከተማ ተገኝተን 10ኛውን የኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች ቀን በዓል ባከበርንበት ወቅት በቀረበው ዝርዝር ዓመታዊ የአፈጻጸም ሪፓርት፣ የየክልሉ ምርጥ ተሞክሮዎች፣ አሰራሮች እና ከአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ የተንፀባረቁ ሐሳቦች ላይ የጋራ ውይይት በማድረግ የሚከተሉትን ባለ10 ነጥብ የጋራ የአቋም መግለጫ አውጥተናል፡፡

1. የፌዴራል መንግሥት፣ የአርብቶ አደር ክልል መንግሥታትና ሌሎችም የሚመለከታችው ሁሉ የአርብቶ አደሩን የልማት ሥራዎች ከማጠናከርና የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ከማሣካት አንፃር በላቀ ቁርጠኝነት ከምንጊዜውም በላይ ተግተው እንዲሠሩ እንጠይቃለን፡

2. በተደጋጋሚ ሲከበሩ በነበሩ የአርብቶ አደር በዓላት ላይ ሲጠየቅ የነበረው የመሬት አጠቃቀም ሥርዓት ተጠንቶ ተግባራዊ እንዲደረግ እንጠይቃለን፣

3. በአርብቶ አደር አካባቢ የተቋቋሙና ወደፊት የሚቋቋሙ የአርብቶ አደር የመማክርት ጉባኤዎች እውቅና አግኝተው እንዲጠናከሩ እንጠይቃለን፣

4. በአርብቶ አደሩ አካባቢ ሠላምን በማረጋገጥ አርብቶ አደሩ ከልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያስችሉ፣ ህብረተሰቡን የሚያሣትፉ፣ የመሠረተ ልማት፣ የማህበራዊ አገልግሎት፣ የመልካም አስተዳደርና የግጭት መከላከል ሥራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ እንጠይቃለን፣

5. መንግሥት በአሁኑ ሰዓት የአርብቶ አደሩን አኗኗርና ውስብስብ ችግሮችን ግምት ውስጥ በማስገባት እያደረገ ያለው የበጀት ምደባ እንዲሻሻል እንጠይቃለን፣

6. በአርብቶ አደሩ አካባቢ እየተተገበሩ ያሉ የእርዳታ ኘሮግራሞች የትኩረት አቅጣጫ ከአርብቶ አደሩ የአኗኗር ዘይቤ ጋር የተጣጣሙና እየታዩ ያሉ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ለይተው ይበልጥ ትኩረት የሚሰጡ እንዲሆኑ እንጠይቃለን፣

7. በአርብቶ አደሩ አካባቢ የሚፈሱ ወንዞችና ሌሎች የውሀ ሀብት ምንጮችን መሠረት ያደረጉ የመስኖ ልማት ሥራዎችን በማጠናከር የአርብቶ አደሩ የገቢ ምንጭ የሚሰፋበትን ሁኔታ በመፍጠር በኩል መንግሥት እያደረገ ያለው ጥረት ተጠናክሮ እንዲቀጥል እንጠይቃለን፣

8. የአርብቶ አደሩን የእንስሳት ሀብት መሠረት ያደረጉ የአርብቶ አደር ኤክስቴንሽንና ምርምር ሥራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ እንጠይቃለን፣

9. መንግሥት ለአርብቶ አደሩ አካባቢ በሁሉም መስክ የሰጠው ልዩና አበረታች ትኩረት ይበልጥ ተጠናክሮ እንዲቀጥል እንጠይቃለን፣

10. ቀደም ሲል ሲከበሩ የነበሩ የአርብቶ አደር በዓሎች በጊዜያዊነት በተቋቋመ ኮሚቴ ሲመራ እንደነበር ይታወሳል፡፡ ይሁን እንጂ ለበለጠ አሠራር ያመች ዘንድ ካሁን በኋላ ያሉ በዓሎች የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር በባለቤትነት ሙሉ በሙሉ ተረክቦ እንዲመራና እንዲያስተባብረው ከአደራ ጭምር እንጠይቃለን፡፡